# <u>ጥላሁን እና ይህ ትውልድ</u>

ከአገር ከሀደት ጣሩር ፣ ከውርደት ውሽንፍር
ከሚዘንበው ሀሰት ፣ ከሚነፍሰው ነውር
ለአገር ጥላ ሆነህ  በመረዋ ድምጽህ
ክብርህ ሳይነካ በክብር ተለየህ።

ስንት ቅኔ መጣ ስንቱ ተገሰሰ
ስንት ድምጽ ሰማን ዚሞም አለቀሰ
ግና አንተ ጣራ ነህ አንተን ማን ደረሰ?!

ጣራ!
ሽቅብ ከአናት በላይ እጅግ የማይደርሱት
ጥላነህ አለኝታ ሁሉን የሚመክት
ስራህ ዘመን የለሽ ስጋህ ግን የሚሞት።

ይህ ትውልድ ቢቸገር ውስጡ ጥበብ ሊያፈልቅ
ከዘራኸው ዜማ በአመታት ከማይደርቅ
ሳታወርሰው ወርሶ በአንተ ዜማ ሲያድግ
አንተ አዲስ ጥበብ ልትሰራ ስትፈልግ
ሙቱ ሞት ቀደመህ ቃልህን ሊያሳርግ።

ውበትን አድማቂ ከደስታ እስከችግር
ያልዳሰስኸው የለ የህይወት ጉራንጉር
ሁሉም ማሳረጊያው የእናት አገር ፍቅር።

ዝናው ያልገደለው በቃሉ ያልታማ
በሄደበት ሁሉ ማእረጉ ከማማ
አንዴም ያልተጠራ በነውር በክፋት
ነፍስና ስጋውን ጥበብ የከበባት
የሙዚቃ ንጉስ ወደር የማይኖረው
የሞትህ አንተ ሳትሆን በስባሹ ስጋህ ነው።

በዳንስህ ማራኪ ግሩም ተንቀሳቃሽ
ለተራብ ለማኝ ለአገር ፍቅር አልቃሽ
ይቅርታን ሰባኪ 'የፍቅር 'መልክት አድራሽ
ጥበብን ያልከዳህ ከሃቅ የማትል ገሽ
እንዴት ሞትህ ይባላል በስጋህ ብትሸሽ?!

ብቻ ይሄ ትውልድ **ከአንተ አንተን ወርሶ**
ከጥበብህ ቀምሶ በዜማህ ደንሶ
ስራህ ይሚገተው በከንቱ እንዳይቀር
እንዲወርስ ያድርገውን የኢትዮጵያን ፍቅር።

በከፍያለው ፈንቴ